# የቅዱሳት መጻሕፍት ስሕተት የለሽነት የቺካጎ መግለጫ

(ርእስ ቁ.1)

የቅጂ መብት 1978 አይሲቢአይ፣ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡ የአይሲቢአይ መዝገብ ማከማቻ ከሆነው የዳላስ ቲዎሎጂካል ሴሚናሪ መዝገብ ቤት በፈቃድ የታተመ

## መቅድም

የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን አሁንንና በማንኛውም ዘመን ለቤተ ክርስቲያን ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ አዳኝና ጌታ አምነው የተቀበሉ ሁሉ የደቀ መዝሙርነታቸውን እውነታ ለተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል በትህትናና በታማኝነት በመታዘዝ ሊያሳዩ ተጠርተዋል፡፡ በእምነትና በባሕሪ ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጪ መሆን ለጌታችን አለመገዛት ነው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ እውነተኛነትንና ታማኝነትን መገንዘብ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥልጣናዊነቱ በበቂ ሁኔታ የሚናገረውን ለማወቅ ወሳኝ ነው፡፡

የሚቀጥለው መግለጫ ይህንኑ የቅዱሳት መጻሕፍት ስሕተት የለሽነት በሚመለከት ያለንን ግንዛቤ ግልጽ በማድረግና በማናምናቸውም ጉዳዮች ማሳሰቢያ በማቅረብ በአዲስ መልኩ ያረጋግጥልናል፡፡  ይህንን መካድ ማለት የመንፈስ ቅዱስንና የኢየሱስን ምስክርነት አለመቀበል  እንዲሁም የእውነተኛ ክርስትና  ምልክት የሆነው ራሱ የእግዚአብሔር ቃል ለሚያዘው አለመገዛት እንደ ሆነ አምነናል፡፡ በክርስቲያን ወገኖቻችን መካከል የመጽሐፍ ቅዱስ ስሕተት የለሽነትን በሚመለከት ከመስመር የለቀቁ አካሔዶች ባሉበት ወቅትና ብሎም ይህ አስተምህሮ በዓለም ዙሪያ ካለው የተሣሣተ ግንዛቤ አንጻር ይህንን የእምነት መግለጫ ማቅረባችን ወቅታዊ እንደሆነ እናምናለን፡፡ ይህ መግለጫ ሦስት ክፍሎች አሉት፡- አጭር መግለጫ፣ የምናምናቸውና የማናምናቸው አንቀጾች እንዲሁም በዚህ ሰነድ ያልተካተተ የሰነዱ አባሪ ማብራሪያ ናቸው፡፡ ይህ መግለጫ የተዘጋጀው በቺካጎ በተካሔደው የሦስት ቀን የመማከርት ጉባኤ ወቅት ነው፡፡ አንቀጾቹንና አጭር መግለጫውን ያጸደቁት ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ስሕተት የለሽነት ያላቸውን እምነት በማጽናት እርስ በርሳቸውም ሆነ ሌሎቹንም ክርስቲኖች በዚህ አስተምህሮ እንዲያድጉና እዲያደንቁትም ያበረታታሉ፡፡ ጠለቅ ባላለና በአጭር ጊዜ  ኮንፈረንስ የሚዘጋጅ እንዲህ ያለ ሰነድ ያለውን ውሱንነት እንገነዘባለን፣ ስለዚህ ይህ መግለጫ የቀኖናት ያህል ክብደት ይሰጠው አንልም፡፡ ይሁን እንጂ እርስ በርስ በነበረን ውይይት ግንዛቤአችን ጥልቀት እንዲኖረው በማድረጉ ደስ እያለን ይህ መግለጫ ለቤተ ክርስቲያን የእምነት፣ የሕይወትና የተልእኮ ተሐድሶ ለእግዚአብሔርም ክብር እንዲሆን አጽድቀነዋል፡፡

እኛ ካቀረብነው ከዚህ መግለጫ የሚነሳ ማንኛውም ውይይት በእግዚአብሔር ጸጋ ሊያጠናክረው እንዲችል በማሰብ በትሕትናና በፍቅር እንጂ በፉክክር መንፈስ ይህንን መግለጫ አላቀረብንም፡፡ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ስሕተት የለሽነት የምናምነውን የማያምኑ በሌላው እምነቶቻቸውና ባሕሪዎቻቸው ይህንን ባለማመን የሚከሰቱ ውጤቶች ያልታየባቸው እንደሚሆኑም እናውቃለን፡፡ እኛም ይህንን አስተምህሮ የተቀበልንንና የምናምን በሐሳብና በድርጊታችን ብዙ ጊዜ ስንክደው እደምንገኝና ባሕልና ልምዶቻችንንም ለዚህ የመለኮት ቃል እንዲገዙ አለማድረጋችንንም እናውቃለን፡፡

በሥልጣኑ ሥር አድረን የምንናገርለትን መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ብርሃን ለመረዳት ይህንንም መግለጫ ለማጠናከር የሚጠቅሙ ሐሳቦችን ለመቀበል እንጋብዛለን፡፡ እኛ ይህንን ምሥክርነት ስንሰጥ ስሕተት የለሽ ነን አንልም፣ ስለዚህ ለእግዚአብሔር ቃል የምንሰጠውን ይህንን ምሥክርነታችንን ለማጠናከር የሚረዳንና ማንኛውንም ገንቢ ሐሳብ በምስጋና እንቀበላለን፡፡

## *አጭር መግለጫ*

1. ራሱ እውነት የሆነውና እውነት ብቻ የሚናገረው እግዚአብሔር ለጠፋው የሰው ልጅ ራሱን በክርስቶስ ኢየሱስ እንደ ፈጣሪነቱ፣ ጌትነቱ፣ አዳኝና ፈራጅነቱ ለመግለጥ የቅዱሳት መጻሕፍትን አብርሖት ሰጥቷል፡፡

2. የእግዚአብሔር የራሱ ቃል የሆነ፣ በመንፈስ ቅዱስም ተቆጣጣሪነት በሰዎች የተዘጋጀው መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረው ትምህርት ሁሉ እንከን የለሽ የመለኮት ሥልጣን ያለው ስለ ሆነ በሚናገረው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር መመሪያ እንደ ሆነ ሊታመን፣ እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝነቱም የሚጠብቅብንን ሁሉ ልንታዘዘው፣ የሚሰጠውንም የተስፋ ቃል እንደ መያዣ ልንቀበለው ይገባል፡፡

3. የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲ የሆነው መለኮት መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን እየመሰከረልን ቃሉን እንድንቀበለውና ትርጉሙን እንድንረዳ አእምሮአችንን ይከፍትልናል፡፡

4. መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉና ቃል በቃል ከእግዚአብሔር የተሰጠ እንደ መሆኑ እግዚአብሔር በፍጥረት ተግባሩ፣ በሚናገረው የዓለም ታሪክ ምስክርነቱ፣ ጽሑፉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር መጀመሩንም በሚመለከት ያለው ትምህርት ሰዎች በእግዚአብሔር ጸጋ እንደሚድኑ ከሚናገረው እውነተኛ ምስክርነት እኩል ስህተትና እንከን የሌለው ነው፡፡

5. ይህ የቅዱሳት መጻሕፍት ፍጹም ስህተት የለሽነት በማንኛውም ዓይነት መልኩ ቢገደብና ችላ ቢባል ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ራሱ ከሚናገረው እውነት በተቃራኒው ካለ አንጻራዊ እውነት አኳያ ከታየ ልናመልጠው በማንችል መልኩ ኃይሉ ይዳከማል፣ ይህንንም የሚቀበሉ ግለሰቦችና ቤተ ክርስቲያንም ከፍተኛ ኪሣራ ይገጥማቸዋል፡፡

### *የምናምናቸውና የማናምናቸው አንቀጾች*

### አንቀጽ አንድ
*መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሥልጣናዊ የእግዚአብሔር ቃል ተቀባይነት ሊያገኝ እንደሚገባ* ***እናምናለን***
*ቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣናቸውን ያገኙት ከቤተ ክርስቲያን፣ ከትውፊትና ከሌሎች ሰብአዊ ምንጮች እንደ ሆነ* ***አናምንም***

### አንቀጽ ሁለት
*መጽሐፍ ቅዱስ ኅሊናን የሚዳኝ የመጨረሻው የጽሑፍ ሥልጣን እንደሆነና የቤተ ክርስቲያንም ሥልጣን ለመጽሐፍ ቅዱስ ተገዢ እንደሆነ* ***እናምናለን፡፡***
የቤተ ክርስቲያን ቀኖናት፣ ጉባኤዎች እና የአቋም መግለጫዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል ወይም የሚበልጥ ሥልጣን እንዳላቸው **አናምንም**

### አንቀጽ ሦስት
የተጻፈው ቃሉ ሙሉ በሙሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠ መገለጥ እንደ ሆነ **እናምናለን፡፡**
*መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር መገለጥ ምስክር ወይም ስናነበው ብቻ መገለጥ የሚሆን ወይም ደግሞ ተቀባይነቱ በሰዎች ምላሽ የሚወሰን እንደሆነ* ***አናምንም፡፡***

### አንቀጽ አራት
እግዚአብሔር በአምሳሉ የፈጠረውን የሰው ልጆችን ቋንቋቸውን ለአሰተርእዮ/ለመገለጥ እንደተጠቀመበት **እናምናለን፡፡**
በፍጥረታዊነቱ ካለበት ውሱንነት የተነሳ የሰብአውያን ቋንቋ ለመለኮታዊ መገለጥ ብቁ እንዳልሆነ **አናምንም**፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በኃጢአት የተነሣ የተበላሸው የሰብአውያን ቋንቋና ባሕል የእግዚአብሔርን የመገለጥ ሥራ አበላሽቷል ብለን **አናምንም፡፡**

## አንቀጽ አምስት
በቅዱሳት መጻሕፍት ያለው የእግዚአብሔር መገለጥ እያደገና እየገሰገሰ የሔደ መሆኑን **እናምናለን፡፡**
ቀድሞ የተሰጠውን መገለጥ ተፈጻሚ የሚደርጉ ተከታይ የሆኑ መገለጦች ነባሩን የሚያስተካክሉ ወይም የሚቃረኑ እንደሆነ **አናምንም፡፡** ከዚህም በተጨማሪ ከአዲስ ኪዳን ጽሑፎች መጠናቀቅ በኋላ ሥልጣናዊ ተቀባይነት ያለው መገለጥ ተሰጥቷል ብለን **አናምንም፡፡**

## አንቀጽ ስድስት
ቅዱሳት መጻሕፍት ሙሉ በሙሉና እያንዳንዱ ክፍል፣ በበኩረ ጽሑፉም ያሉ እያንዳንዱ ቃላትም በመለኮት እስትንፋስ የተሰጡ ናቸው ብለን **እናምናለን**፡፡
የቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ መለኮትነት አጠቃላዩን እንጂ በከፊል ወይም ደግሞ ከፊሉን እንጂ አጠቃላዩን አይደለም በማለት **አናምንም**

## አንቀጽ ሰባት
እስትንፋሰ መለኮት በሰብአውያን ጸሐፊዎች በኩል ቃሉን የሰጠበት የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሥራ እንደ ሆነ **እናምለን**፡፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ጅማሬ መለኮታዊ ነው፡፡ ቀሪው የእስትንፋሰ መለኮት አፈጻጸም በአብዛኛው ለእኛ ምስጢር ነው፡፡
እስትፋሰ መለኮት የሰብአውያን ብሩህ መገለጥ ወይም ከፍ ያለ የኅሊና ደረጃ ውጤት እንደ ሆነ **አናምንም፡፡**

## አንቀጽ ስምንት
እግዚአብሔር በመለኮት ሥራው መርጦ ያዘጋጃቸውን የጸሐፊዎቹን ባሕሪያትና የጽሑፋቸውን ዘይቤ እንደተጠቀመበት **እናምናለን**፡፡
እግዚአብሔር እርሱ የመረጣቸውን ቃላት ይጠቀሙ ዘንድ የጸሐፊዎቹን ማንነት አልፎ ሔዷል ብለን **አናምንም፡፡**

## አንቀጽ ዘጠኝ
እስትንፋሰ መለኮት ሁሉን አዋቂነትን ባይሰጥም የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች የተናገሩትንና የጻፉትን በሚመለከት እውነተኛነትንና ተአማኒነትን እንደሰጣቸው **እናምናለን፡፡**
የጸሐፊዎቹ ውሱንነትና ኃጢአተኛ ተፈጥሮ የግድ ወይም በማንኛውም መልኩ የእግዚአብሔርን ቃል እንዳጣመመ ወይም እንዳሳሳተ **አናምንም፡፡**

## አንቀጽ አስር
በቀጥተኛ ንግግር እስትንፋሰ መለኮት የቅዱሳት መጻሕፍት በኩረ ጽሑፎችን የሚመለከት ሲሆን በእግዚአብሔር መጋቢነት የተነሣ በበቂ ትክክለኛነት ካሉን ቅጂዎች መረዳት እንደምንችል እናምናለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቅዱሳት መጻሕፍት ቅጂዎችና ትርጉሞች የእግዚአብሔር ቃል መሆናቸውንና በኩረ ጽሑፉንም የሚወክሉ መሆናቸውን **እናምናለን፡፡**
በኩረ ጽሑፍ ባለመኖሩ በክርስትና እምነት አብይ የሆኑ ጉዳዮችን ጎድቷል ብለን **አናምንም**፡፡ በተጨማሪም በኩረ ጽሑፍ ባለመኖሩ የቅዱሳት መጻሕፍት ስህተት የለሽነት አስተምህሮን ከንቱ ያደርገዋል ብለን **አናምንም፡፡**

## አንቀጽ አስራ አንድ
መጽሐፍ ቅዱስ በእስትንፋሰ መለኮት አማካኝነት የተሰጠ በመሆኑ እኛን የማያሳስት በሚያቀርባቸው ርእሰ ጉዳዮችም ሁሉ እውነተኛና ተአማኒ እንደሆነ **እናምለን፡፡**
መጽሐፍ ቅዱስ በሚናገረው ነገር በአንድ ጊዜ ፍጹም የሆነና ስሕተት ያለው ሊሆን ይችላል ብለን **አናምንም፡፡** ፍጹምነትና ስሕተት የለሽነት ተለያይተው ሊታወቁ ይችላሉ ነገር ግን አይነጣጠሉም፡፡

## አንቀጽ አስራ ሁለት
መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ስሕተት የሌለው፣ ከሐሰትም የጸዳ፣ ማሳትና ማሳሳት የሌለበት እንደሆነ **እናምናለን፡፡**
የመጽሐፍ ቅዱስ ስሕተት የለሽነትና ፍጹምነት ታሪክንና ሳይንስን ሳይመለከት ከመንፈሳዊ፣ ሃይማኖታዊና የድነት ታሪኮች ጋር ብቻ የተገናኘ ነው ብለን **አናምንም**፡፡ ስለ መሬት ታሪክ ሳይንሳዊ መላምት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፍጥረትና ስለ ጥፋት ውሃ ለተናገረው ልዋጭ ትምህርት ይሆናል ብለን **አናምንም፡፡**

## አንቀጽ አስራ ሦስት

የቅዱሳት መጻሕፍት ስሕተት የለሽነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ እውነተኛነት ጋር በተያያዥ ጥቅም ላይ የሚውል ነገረ መለኮታዊ ስያሜ ቃል እንደሆነ **እናምናለን፡፡** ቅዱሳት መጻሕፍትን ከአጠቃቀማቸውና ከዓላማቸው ውጪ በዘመናዊ የእቅጭ መለኪያ፣ በሚታዩ ግነታዊ ሐሳቦች፣ በሰዋሰው አለመስተካከል፣ ወይም በቃላት ግድፈት ወይም ተፈጥሮን በማስተዋል በሚደረጉ መግለጫዎች፣ በቁጥር መሸራረፍ፣ በተካተቱ ርእሶች ቅደም ተከተል በመለካት ስለ ስሕተት የለሽነታቸው የሚቀርበውን ተቃውሞ አንቀበልም፣ **እናምንም፡፡**

## አንቀጽ አስራ አራት

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጣዊ አንድነትና ዘላቂነት እንዳለው **እናምናለን፡፡**
አሉ የሚባሉና እስከ አሁንም መፍትሔ ያላገኙ ስሕተት ተብዬዎች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ራሱ የሚናገረውን እውነት ከንቱ ያደርጋሉ ብለን **እናምንም፡፡**

## አንቀጽ አስራ አምስት

የቅዱሳት መጻሕፍት ስሕተት የለሽነት የተመሠረተው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እስትንፋሰ መለኮት በሚያስተምረው ላይ እንደ ሆነ **እናምናለን፡፡**
ኢየሱስ በሥጋው ወራት በነበረው ውሱንነት ተመካኝቶ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተማረውን አንቀበልም የሚለውን ሐሳብ **እናምንም፡፡**

## አንቀጽ አስራ ስድስት

የቅዱሳት መጻሕፍት ስሕተት የለሽነት አስተምህሮ የቤተ ክርስቲያን እምነት ሆኖ በታሪኳ የኖረ እንደ ሆነ **እናምናለን፡፡**
የቅዱሳት መጻሕፍት ስሕተት የለሽነት አስተምህሮ በፕሮቴስታንታዊ ምሁራን የተፈበረከ ከፍ ላሉ ትችቶች የአቋም ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጀ እንደ ሆነ **እናምንም፡፡**

## አንቀጽ አስራ ሰባት

መንፈስ ቅዱስ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት እየመሰከረ ለአማኞች የእግዚአብሔርን ቃል እውነተኛነት ያረጋግጥላቸዋል ብለን **እናምናለን፡፡**
ይህ የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ያለ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሆን ወይም ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር የሚቃረን እንደሚሆን **እናምንም፡፡**

## አንቀጽ አስራ ስምንት

የቅዱሳት መጻሕፍት ንባባት ሰዋሰዋዊና-ታሪካዊ አፈታት ሊደረግባቸው እንደሚገባና ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጻቸውን ከግምት ውስጥ በመክተትና መጽሐፍ ቅዱስም ራሱን በራሱ በማመሳከር መተርጎም እንዳለበት **እናምናለን፡፡**
ንባባቱ ከየት መጡ በማለት ተቀባይነታቸውን አንጻራዊ የሚያደርግና ከታሪካቸው ዐውድ እንዲወጡ ወይም ትምህርታቸውና ጸሐፊዎቻቸው ተቀባይነት እንዲያጡ የሚያደርጉ አቀራረቦችን **እናምንም፡፡**

## አንቀጽ አስራ ዘጠኝ

የቅዱሳት መጻሕፍትን ሙሉ ሥልጣናዊነት፣ ፍጹምነትና ስሕተት የለሽነትን ማመን መላው የክርስትና እምነትን በሚገባ ለመረዳት እጅግ ወሳኝ እንደሆነ **እናምናለን፡፡** በተጨማሪም ይህ እምነት ክርስቶስን ወደ መምሰል ያሳድጋል ብለን **እናምናለን፡፡**
ይህንን እምነት ለደኅንነት ያስፈልጋል ብለን **እናምንም፣** ይሁን እንጂ የቅዱሳት መጻሕፍት ስሕተት የለሽነትን አንቀበልም ማለት ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለግለሰቦች አስከፊ ውጤት አያስከትልም ብለን **እናምንም፡፡**